# ***ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ፣ አመክንዮአዊ የሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ)፦ ምንነቱና መገለጫዎቹ***


አልዩ አባተ ይማም*



**አህጽሮተ-ጽሁፍ**

የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት ከመጽደቁ በፊት ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ፍ/ቤቶች፣ በፌዴራል እና የክልል ሕግ አውጪ ምክር ቤቶች እውቅና ሊሰጣቸውና ሊደራጁ እንደሚገባ የኢፌዲሪ ሕግ መንግሥት አንቀጽ 78(5) በሚያስገድደው *መሠረት*፣ ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ በሃገሪቱ ሲሰራባቸው የነበሩ የሸሪዓ ፍ/ቤቶች፣ በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የአቋም ማጠናከሪያ አዋጆች ወጥተው፣ ከመጀመሪያ ደረጃ እስከ ጠቅላይ ፍ/ቤት ድረስ እንደገና ተደራጅተው በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ፍ/ቤቶቹ በባለጉዳዮች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው ሲሆን፣ የሚቀርቡላቸውን የግልና የቤተሰብ ግጭቶችን የሸሪዓ ሕግን ተፈጻሚ በማድረግ እልባት ይሰጣሉ፡፡ የሸሪዓ  ሕግ ምንጮች በጥቅሉ ሦስት ናቸው፤ እነሱም ቁርአን፣ *ሱናሕ* እና *ኢጅቲሓድ* (አመክንዮአዊ ምርምር) ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት የሸሪዓ ቀዳሚ ምንጮች በመለኮታዊ ራዕይ *(ወህይ)* የተገለጹ ሲሆን፣ በግልና በቤተሰብ ግንኙነቶች ላይ ቁጥራቸው ጥቂት የሚባሉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተቱ ሲሆን፣ አብዛህኞቹ የቁርአንና የ*ሱናሕ* ሕጎች የጥቅልነት ባህሪ ያላቸው እና በልዩ ልዩ የሕግ ዘርፎች ላይ አጠቃላይ እና ንዑስ የሸሪዓ ዓላማዎችን የሚቀይሱ ናቸው፡፡ ይህ ገጽታቸው፣ ዝርዝር የሸሪዓ ሕግ ማዕቀፍ *(ፊቅሕ)* እንደ ወቅቱ እና ማህበረሰቡ ተጨባጭ እውነታ፣ በሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* አማካይነት እንዲዳብር መሠረት ጥሏል፡፡ በመሆኑም፣ *ኢጅቲሓድ*፣ በየትኛውም የሕግ መስክ ላይ የሸሪዓ ዝርዝር ሕግጋት ለመቅረጽ ዋነኛ ምንጭ በመሆን ሰፊውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ስለዚህ፣ *ኢጅቲሓድ* ዋነኛ የሸሪዓ ሕግ ምንጭ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ምንነቱን እና መሠረታዊ መገለጫዎቹን በተመለከተ በመስኩ ምሁራን የሚነሱ ፍሬ-ሐሳቦች እና ጭብጦች በዚህ ጽሁፍ ተዳሰዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሕግ አተረጓጎም ጋር በተያየዘ፣ የሃገሪቱን ሙስሊም ማህበረሰብ ነባራዊ ሐቆች እና አካባቢያዊ እውነታዎች ያገናዘበ ትክክለኛና ተገቢ የሆነ የሸሪዓ ሕግ አተረጓጎምና አፈጻጸም እውን ለማድረግ፣ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በ*ኢጅቲሓድ*አማካይነት ማሻሻያዎችንና አዲስ የሸሪዓ ብይኖችን ለማስተዋወቅ ይቻል ዘንድ፣ በ*ኢጅቲሓድ*እና በመርሆዎቹ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ መጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ ሸሪዓን በትክክል ለመረዳት፣ ገዢነቱ በጊዜ እና በሕብረተስብ እውነታዎች ሳይገደብ፣ ተለማጭነቱን ማረጋገጥና የፍትሕ ዓላማዎቹን ማሳካት የሚቻለው በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት በመሆኑ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት አግባብነት ያላቸውን የሸሪዓ የግልና የቤተሰብ ሕጎችን፣ እንዲሁም የኢስላም የፋይናንስና የባንክ ድንጋጌዎችና አሰራሮችን ከሃገሪቱ ተጨባጭ ጋር እንዲጣጣሙ በማድረግ ረገድ ወደፊት ለሚደረገው የሕግ አወጣጥ፣ ዳኝነትና ግጭት አፈታት እነዲሁም ጥናትና ምርምር ምንጭ እና መሪ በመሆን የሚያገለግለው *ኢጅቲሓድ* በመሆኑ፣ ይህ ጽኁፍ በዚህ ወሳኝ የሸሪዓ ሕግ ምንጭ ዙሪያ መሠረታዊ ግንዛቤ የሚያስጨብጭ ማብራሪያ ያቀርባል፡፡



**ቁልፍ ቃላት**

*ኢጅቲሓድ*፤ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር፤ አመክንዮ፤ የሸሪዓ ምንጭ፣ የግል አስተያየት፤ ሸሪዓ፤ *ፊቅሕ፤ ሙጅተሒድ፣*


## 1. *መግቢያ*

*ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር (ኢጅቲሓድ) ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ መሆኑን እና ዝርዝር የሸሪዓ ሕግጋትን በመቅረጽ ረገድ ሰፊ ድርሻ ያለው ከመሆኑ አንጻር ምንነቱን፣ ንድፈ-ሐሳቦቹን፣ የምርምር ዘዴዎችንና ሥነ-ሥርዓት እንዲሁም ሌሎች በርዕሱ ሥር የሚነሱ መሠረታዊ ፍሬ-ሐሳቦችንና ጭብጦችን የሚዳስስ ጽኁፍ ለኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ያለው አግባብነትና ጠቀሜታ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ለዚህ ምላሹ ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ማቋቋሚያ ሠነድ ከሆነው የፌዴራል ሕገ መንግሥት አንቀጾች የሚገኝ ነው፡፡*[1] በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 34(5) እና 78 (5) እንደተደነገገው፣ ከኦፌሴላዊ የመንግሥት የሕግና ፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ እውቅና ሊሰጣቸው የሚችሉ የሕግ ሥርዓቶች አሉ፤ እነሱም ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ሕጎች ናቸው፡፡ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለሚነሱ ግላዊና እና የቤተሰብ ግጭቶች፣ በባለጉዳዮቹ ፈቃድ በባህል ወይም በሃይማኖት ሕጎች መሠረት ሊዳኝ እና እልባት ሊሰጣቸው እንደሚችል ሕገ-መንግሥቱ ይደነግጋል፡፡

---


* ኤል.ኤል.ቢ፣ ኤል.ኤል.ኤም. በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሕግ እጩ ዶክተር፣ ጸሐፊውን በኢ-ሜይል አድራሻ alyuabate09@gmail.com ማግኘት ይቻላል፡፡


[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዲሪ) ሕገ-መንግሥት፣ 1987 ዓም፣ ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ቁጥር 1

ሸሪዓዊ የግጭት አፈታት ተቋማዊ አደረጃጀትን በተመለከተ፣ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(4) ላይ እንደተመለከተው፣ የግልና የቤተሰብ ግጭቶችን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ ፍ/ቤቶችን የማቋቋም ሥልጣን ለፌዴሬሽኑ የሕግ አውጪ አካላት፣ ማለትም በፌዴራል ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በክልሎች ደረጃ ደግሞ ለክልል ምክር-ቤቶች ተሰጥቷል፡፡ በዚህ የሕገ-መንግሥት ድንጋጌ መሠረት፣ የባህል እና የሐይማኖት ፍ/ቤቶችን የማቋቋም ጥያቄዎችን ተቀብሎና ገምግሞ፣ በቂ ፍላጎት ያለና አስፈላጊነቱ የታመነበት ከሆነ፣ በሕግ አውጪዎቹ ይሁንታ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ፍ/ቤቶች ተቋቁመው የሕግ ብዝኃነቱ አካልና ተዋናይ እንዲሆኑ ሊደረግ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ከመደበኛ ፍ/ቤቶች ውጪ ያሉ የዳኝነት አካላት የሚቋቋሙበት ይህ ሥርዓት፣ ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች ተፈጻሚ አይሆንም፤ ምክንያቱ ደግሞ በአንቀጹ ንዑስ 5 ይገኛል፡፡ ይኸውም ሕገ-መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የባህል ወይም የሃይማኖት ፍ/ቤቶች እውቅና አግኘተው እንዲደራጁ የሚያስገድድ በመሆኑ ነዉ፡፡ በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ታሪክ ደግሞ፣ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ከአፄ ሐይለ-ሥላሴ ሥርዓተ-መንግሥት በፊት ጀምሮ በሥራ ላይ የነበሩ በመሆኑ፣[2] በንጉሱ ዘመን የቃዲና የናኢባ ፍ/ቤቶች ተብለው በ1934 እና በ1936 በወጡ የማቋቋሚያና የማሻሻያ አዋጆች ተደራጅተው ሲሰሩ የነበሩ ናቸው፡፡[3] ስለሆነም ሸሪዓ ፍ/ቤቶች፣ ከመንግሥታዊ የዳኝነት ተቋማት በተጓዳኝ በመሥራት ከሕገ-መንግሥቱ መጽደቅ በፊት ሲሠሩ የነበሩ በመሆኑ እነዚህን ፍ/ቤቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ አቋቋሞ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ማድረግ በሕግ አውጪዎች ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ ሕገ-መንግሥቱ ራሱ ያቋቋማቸው እና እውቅና ማግኘታቸው በሕግ አውጪ አካላት ላይ የተጣለ ሕገ-መንግሥታዊ ግዴታ መሆኑን ይገነዘቧል፡፡

የፌዴራል ሕግ-መንግሥቱን አስገዳጅ አንቀጽ መሠረት በማድረግ፣ የፌዴራልና የክልል ም/ቤቶች የሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም የሚያጠናክሩ እና እንደገና የሚያደራጁ አዋጆችን አዉጥተዋል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፣ ‹የፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶችን አቋም ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 188/1992› የተሰኘ አዋጅ አውጥቶ፣ ፍ/ቤቶቹ በይበልጥ ተጠናክረውና ተደራጅተው እየሰሩ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ በተመሳሳይ የክልል መንግሥታትም በበኩላቸዉ የፌዴራል ሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 78(5) መነሻ በማድረግ፣ ክልላዊ ተፈጻሚነት ያላቸው የየራሳቸውን የሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች አውጥተው፣ በሃገሪቱ ዙሪያ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ደረጃ፣ የመጀመሪያ፣ ከፍተኛና ጠቅላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ተደራጅተው በተከራካሪዎች ፈቃድ ላይ ተመርኩዞው በግልና በቤተሰብ ጉዳዮች ላይ ሸሪዓዊ ፍትሕን በማድረስ ላይ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ ይህም ሕጋዊ እውቅና ያገኘ የሕግ ብዝኃነት (*Legal Pluralism*) የሃገሪቱ የሕግ ሥርዓት አካል እንደሰፈነ የሚያሳይ እውነታ ነው፡፡[4]

በፌዴራል ሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ አንቀጽ 3 መሠረት፣ ለሸሪዓ ፍ/ቤቶች የሚቀርቡ ጉዳዮች በሸሪዓ ሕግ መሠረት እንደሚዳኙ ይደነግጋል፡፡ የሸሪዓ ሕግ ደግሞ በጥቅሉ ሁለት ምንጮች አሉት፤ እነሱም ራዕያዊ *(ነቅሊያሕ/revealed)* እና አመክንዮአዊ *(ዐቅሊያሕ/rational)* ምንጮች ናቸው፤ ራዕያዊ ምንጮች በመለኮታዊ ራዕይ *(ወህይ)* የተገለጹ ሲሆኑ፣ ቁርአን እና *ሱናሕ* በዚህ ምድብ ስር ይወድቃሉ፡፡[5] በአመክንዮአዊ የሸሪዓ ምንጮች ሥር ደግሞ በ*መዛሒብ* (የሕግ ት/ቤቶች)

---

[2] ዛኪ ሙስጠፋ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት የእስላም ፍርድ ቤቶች የሚሰራበት ሕግ፤ ለሸሪዓ ሕግ በሥራ ላይ መዋል መቀጠል ምክንያት የሆኑ ነገሮች፣ የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ ቅጽ 9፣ ቁጥር 1፣ 1965፣ ገጽ 173 ይመለከቷል፡፡ See also: Mohammed Abdo, Legal Pluralism, Sharia Courts, And Constitutional Issues in Ethiopia, Mizan Law Review, Vol. 5 No.1 (2011), p. 78.

[3] የቃዲ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 2/1934 እና የቃዲዎችና የናኢባ ምክር-ቤቶች አዋጅ ቁጥር 62/1936፡፡

[4] በሕግ እውቅና ካገኘ የሕግ ብዝኃነት *(De-jure)* በተቃራኒ፣ ሕግ ያልፈቀደውና እውቅና ያልተሰጠው፣ ነባራዊ የሕግ-ብዝኃነት *(De-facto)* አለ፡፡ ይህ የብዝኃነት ጽንሰ-ሐሳብ፣ በአንድ የሕግ ሥርዓት ውስጥ በተጨባጭ የሚታየውን፣ ከመንግሥታዊ የፍትሕ ሥርዓት በተጓዳኝ የግለሰቦችንና የማህበረሰብ ባህርይ እና ምግባር የሚቀርጹና የሚመሩ ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑበትን ተጨባጭ እውነታ የሚያመለክት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የሸሪዓ ሕግ ወይም ባህላዊ ሕጎች በባህላዊ እና ኃይማኖታዊ የፍትሕ ተቋማት አማካይነት ከተፈቀዱበት ወሰን አልፈው በፍትሐ-ብሔራዊ፣ በንግድ እና በወንጀል ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉ መሆኑ የማይካድ ሐቅ ነው፡፡ ከሕግ እውቅና ውጪ የሆነው ነባራዊ ብዝኃነት፣ በሃገራዊ የፍትሕ ሥርዓት፣ በጸታ እኩልነት እና ሰብዓዊ መብት፣ በልማታዊ የፖሊሲ አፈጻጸም እርምጃዎች ላይ የራሱ የሆኑ አሉታዊ ሚናዎች ያሉት ሲሆን፣ ለባህላዊና የሃይማኖት የሕግ ሥርዓቶች የተሰጣቸው የእውቅና ደረጃና የተፈጻሚነት መጠን የተወሰነው፣ ግጭቶችን ለመፍታት ካላቸው ውጤታማነት *(Instrumental Function)*፣ በሰብዓዊ መብቶች፣ በእድገት እና ሥልጣኔ ላይ የሚጋርጧቸው ችግሮች እና ሌሎች ታሳቢዎች ግምት ውስጥ ገብተው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከነዚህ እሳቤዎች አንጻር ደጋፊ ወይም ነቃፊ የመከራከሪያ ሐሳቦች ሊቀርቡ የሚችሉ መሆኑ እና እየቀረቡ ያሉ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

[5] Ahmad Hasan, The Sources of "Fiqh": A General Survey, Islamic Studies, Vol. 29, No. 2 (1990), p.114.

መስራቾችና (*ኢማም/አኢማሕ*) እና የ*ኡሱል ኣል-ፊቅሕ* (የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች) ሊቃውንት የተቀረጹ፣ ለሕግ ምርምር መንደርደሪያና ለዝርዝር ሕጎች ምንጭ የሆኑ ጥቅል የሕግ መርሆዎች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ የኢጅቲሓድ መርሆዎች መካከል ምስስሏዊ አመክንዮ *(ቂያስ/analogy)*፣ የሕዝብ ጥቅም *(መስላሃሕ/Public Interest)*፣ ከምንጩ ማድረቅ (*ሰድ አዝ-ዘራኢዕ/* Blocking the Means)፣ ርትዕ *(ኢስቲህሳን/Equity)* ወዘተ. ይገኙበታል፡፡[6]

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ እነዚህን *የኢጅቲሓድ* ንድፈ-ሐሳቦች መተንተን ሳይሆን፣ የራሱን *የኢጅቲሓድን* ምንነት እና ከሕግ ምንጭነቱ ጋር ተያይዞ በመስኩ የሚነሱ አጠቃላይ ነጥቦችን መዳሰስ ነው፡፡ በቁርአንና *ሱናሕ* የሚገኙ የዝርዝር ድንጋጌዎች አተረጓጎም እና አዳዲስ ሕግጋት ለመቅረጽ መነሻ የሆኑ ኢጅቲሓዳዊ ንድፈ-ሐሳቦች ምናልባትም በሌላ ጽሁፍ የሚዳሰሱ ርዕሰ-ጉዳዮች ይሆናሉ፡፡

## 2. *የኢጅቲሓድ ምንነት*

የሸሪዓ ሕግ ምንጮች ራዕያዊ እና አመክንዮአዊ ተብለው በሁለት ጥቅል ምድቦች ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፤ ራዕያዊ የሚባሉት ምንጫቸው ከአምላክ ነው ተብለው የሚታመኑትን ቁርአን እና *ሱናሕን* የሚይዝ ሲሆን፣ በእነዚህ ቀዳሚ መለኮታዊ የሕግ ምንጮች በግልጽ ያልተሸፈኑ ወይም ከነአካቴው ያልተነሱ ጉዳዮች ላይ ጥቅል የሕግ መርሆዎችና እና ገዢ የሆኑ ዝርዝር ድንጋጌዎች የሚለዩበት ዘዴ ወይም ምንጭ አመክንዮአዊ የሸሪዓ ምርምር ወይም ኢጅቲሓድ ይባላል፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ኢጅቲሓድ ማለት ከቀዳሚ የቁርአንና *ሱናሕ* የሕግ መርሆዎችና ልዩ ድንጋጌዎች በመነሳት አዳዲስ ሕጎች የሚቀረጹበት፣ የነባር ሕጎች አተረጓጎምና አፈጻጸም የሚታረቅበት ምሁራዊ የሕግ ምርምር ጥረት ነው፡፡[7] *ኢጅቲሓድ* ሥርወ-ቃሉ ‹*ጃሕዳሕ*› ሲሆን ትርጉሙም ጥረት፣ ልፋት፣ ትግል ማለት ሲሆን በሸሪዓ የሕግ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ ሲውል ደግሞ ከቋንቋዊ ትርጓሜው በጠበበ መልኩ፣ ሕግጋትን ለመተርጎምና ለመቅረጽ የሚደረግን አዕምሯዊ ጥረት ያመለክታል፡፡ *ኢጅቲሓድ* ማለት በምንጮች ላይ በመመርኮዝ ግልጽ የሸሪዓ ድንጋጌ በሌለባቸው የሕግ ጭብጦች ላይ ገዢ የሆነውን ድንጋጌ ለመለየት የሚደረግ ከፍተኛ የሕግ የምርምር *(ኢስቲንባጥ)* ሒደት ነው፡፡[8]

*ኢጅቲሓድ* ማለት ለአዲስ ጭብጥ የሕግ እልባት ለመስጠት ቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮችን በማጣቀስ ልዩ ድንጋጌ (ድምዳሜ - *ሁክም*) ላይ ለመድረስ የሚደረግ አመክንዮአዊ የሕግ ምርምር ወይም ሕግን የመቅሰም ጥረት እንደሆነ ከላይ ተገልጿል፡፡ ይህ ትርጓሜ፣ ሸሪዓዊ ምርምር የዘመኑን ሙስሊም ማህበረሰብ ተጨባጭ እውነታዎች ያገናዘበ መሆን ያለበት ከመሆኑ አኳያ፣ በቀደመው *ኡሱል ኣል-ፊቅሕ* ጥናት ውስጥ ለኢጅቲሓድ ይሰጠው የነበረውን ትርጓሜ ሊሻሻል እንደሚገባ፣ በተለይም ከዚህ ከነባራዊነት ገጽታው በተጨማሪ፣ በግለሰብ ሊቃውንት ይዞታነት በተጨማሪ በሕብረት ሊተገበር የሚችል *(ኢጅቲሓድ ጀማዒ)* እንደሆነ የሚያስረዳ አዲስ ትርጓሜ ሊሰጠው እንደሚገባ ፕሮፌሰር ከማሊ፣ *Shariah Law: An Introduction* በተሰኘ መጽሃፋቸው ያስገነዝባሉ፡፡[9] ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፣ ከነባሩ *የኢጅቲሓድ* አረዳድ በተጨማሪ ሁለት ምልከታዎች የትርጓሜው አካል መደረግ ይኖርባቸዋል፤ እነዚህም አንደኛ፣ *ኢጅቲሓድ* በቀደሙት ዘመናት በዋናነት በግለሰብ ደረጃ በሸሪዓ ሊቆች ሲተገበር የነበረ በመሆኑ፣ በመንግሥት የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ ተቋማዊ አደረጃጀት ያላገኘና በየዘመናቱ የነበሩ የ*ኡሱል* እና የ*ፊቅሕ* ሊቃውንት በግላቸው የየራሳቸውን ምርምር በማድረግና *ፈትዋ* (ድምዳሜ) በመስጠት ላይ የተወሰነ ስለነበር ዘመናዊው የመንግሥት አወቃቀር፣ የሕግ አወጣጥ እና የዳኝነት ሥርዓት ጋር ተጣጥሞ ይተገበር ዘንድ የሕብረት *ኢጅቲሓድ (ኢጅቲሓድ ጀማዒ)* ወይም ተቋማዊ ማዕቀፍ ያለው ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር ሂደት ሊዳብር ይገባል፣ የትርጓሜውም አካል መሆን አለበት፡፡ ሁለተኛ፣ የ21ኛው ክፍለ-ዘመን ሙስሊም ማህበረሰቦችን ዘርፈ-ብዙና ውስብስብ ግንኙነቶችን የሚገዛ የሕግ ማዕቀፍ ለመቅረጽ የሚቻለው በሁሉም ግላዊና ማህበረሰባዊ መስተጋብሮች ላይ ጥልቅ ጥናት ሲደረግ እና በቂ እውቀት ሲኖር ነው፡፡ ይህ በሌለበት ሕብረተሰቡን ወደ ተሻለ ሁኔታ የሚመራ የሕግ ማዕቀፍ ማበጀት የማይቻል በመሆኑ፣ ሸሪዓዊ የሕግ

[6] Ibid., p. 115.

[7] Mohamed Abdel-Khalek Omar, Reasoning in Islamic Law: Part Two, Arab Law Quarterly, Vol. 12, No. 4 (1997), p. 355.

[8] Mohammad Hashim Kamali, Sharia Law: An Introduction, Oxford:Oneworld Publications, Oxford, 2008, pp. 162-163.

[9] Ibid., p. 165. See also: Mohammad Hashim Kamali, Issues in the Theory of Ijtihad: A Reappraisal, Bulletin on Islam and Cntemporary Issues, No. 29 (2015), International Institute of Advanced Islamic Studies (IAIS) Malaysia, pp. 3-4.

አተረጓጎም እና የሕግ አወጣጥ ሂደት ከጥንታዊ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች እና *ሥነ-ሥርዓት* ግንዛቤ ባሻገር፣ ተመራማሪው *(ሙጀቲሒድ)* *ኢጅቲሓድ* በሚያደርግበት ዘርፍ ላይ ልዩ ሙያዊ እውቀት (Expertise Knowledge) ሊኖረው ይገባል፣ አሊያም የዘርፉን አጥኚዎችና ባለሙያዎች ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ሁለተኛ፣ በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት የሸሪዓ ሕግን ከተለዋዋጭ ነባራዊ እውነታዎች ጋር ማጣጣም፣ እንዲሁም አግባብነቱ እና ገዢነቱ ቀጣይ እንዲሆን ማድረግ የሚቻለው የምርምር ሂደቱ ሃገራዊ፣ ማህበረሰባዊ እና ግላዊ እውነታዎችን ያገናዘበ ሲሆን ነው፡፡ ይህ የነባራዊነት ገጽታ፣ ምንም አንኳ በቀደሚው የ*ኡሱል* ጥናት ላይ ተጠቅሶ የሚታለፍ ቢሆንም፣ የትርጓሜው አካል ሊደረግና እና አጽንኦት ሊያገኝ እንደሚገባ ከማሊ ያስገነዝባሉ፡፡[10] እነዚህ እይታዎች ባከተተ መልክ፣ ከማሊ *ኢጅቲሓድን*እንደሚከተለው ተርጉመውታል፡-[11]

> *ኢጅቲሓድ* ማለት በአንድ አዲስ ጭብጥ ላይ ሸሪዓዊ ብይን ላይ ለመድረስ፣ የሸሪዓ ምንጮችን መሠረት ያደረገ፣ ተጨባጭ ማህበረሰባዊ እውነታዎችን ያገናዘበ፣ ሁሉ-አቀፍ የሆነ እና ጥልቅ ፈጠራዊ እሳቤ የተሞላበት፣ ብቁ በሆኑ ሊቆች በቡድን ወይም በግል የሚደረግ ሁለ-ገብ አመክንዮአዊ የምርምር ጥረት ነው፡፡[12]

በራዕያዊ የሸሪዓ ምንጮች (ቁርአን እና *ሱናሕ)* እና *በኢጅቲሓድ* መካከል ያለው ልዩነት፣ ከላይ በትርጓሜው ውስጥ እንደተመለከተው፣ መለኮታዊ እና ነቢያዊ ድንጋጌዎች በሙሀመድ ሕልፈት የተቋረጡ እና ከዚያ በኋለ መለኮታዊ ነው ሊባል የሚችል የሕግ ድንጋጌ የሌለ ሲሆን፣ *ኢጅቲሓድ* በሕግ ምንጭነቱ ቀጣይ የሆነና በጊዜ ሂደት እየዳበረ፣ እየተሻሻለ የሚሄድ ነው፡፡ *ኢጅቲሓድ* የሸሪዓ ሕግን ከተገለጹ ምንጮች ተቀብሎ፣ አግባብነቱና ተፋጻሚነቱ በጊዜ፣ በቦታ እና በሁኔታ ሳይገደብ ለዘመን እና ለትውልድ ተስማሚ እንዲሆን የሚያደርግ እጅግ ጠቃሚ የሕግ መሣሪያ ነው፡፡[13]

ሌላው የ*ኢጅቲሓድ* መገለጫ፣ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ አመክንዮአዊ ምርምር እንደመሆኑ፣[14] ተቃራኒ ሐሳብ ሊቀርብበት የሚችል፣ አስገዳጅ ያልሆነ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ *(ዞኒ)* የምርምር ሂደት መሆኑ ነው፡፡[15] በተጨማሪም፣ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የሚችለው ግለሰብ በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ላይ ጥልቅ እውቀት ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ፣ ከዚህ እውቀት ላይ በመንደርደር የሐሳብ ትንታኔ *(ኢስቲንባጥ)* ማድረግ በሚችል ተመራማሪ ሊቅ *(ሙጅተሒድ)* ወይም ሊቆች *(ሙጅተሒዱን)* እንጂ የ*ፊቅሕ* እውቀት ያለው ነገር ግን ዘዴያዊ የሕግ ትንታኔ ማድረግ የማይችል፣ አዋቂ *(ዐሊም)* የተባለ ሁሉ የሚያከናውነው አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡[16]

*ኢጅቲሓድ* በምንጭነቱ ከቁርአን እና *ሱናሕ* በጥብቅ የተሳሰረ እና መንደርደሪያ መርሆዎቹ ከቀዳሚ ምንጮች የተገኙ በመሆናቸው ሁሉም የሸሪዓ ምንጮች እርስ-በርስ የተቆራኙ ናቸው፡፡ በተለይም ቀዳሚ እና ተከታይ፣ ወይም የተገለጹ እና

---

[10] Ibid.

[11] Ibid., p. 4

[12] ይህ ትርጓሜ *ኢጅቲሓድ* በዘመኑ የዓለም ሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ሚና የሚያመለክት ነው፡፡ እነዚህ አዳዲስ የ*ኢጅቲሓድ* ገጽታዎች፣ ለ*ኡሱል አል-ፊቅሕ* መስከ አዲስ የእውቀት ጭማሬዎች በመሆናቸው፣ በተለይም *ሙጀተሒዶች* የሸሪዓ ምንጮችን አጣቅሰው *ኢጅቲሓድ* ለማድረግ ሲነሱ፣ የሕጎቹን ዓላማዎችን ያገናዘበ እና ግቦችን የሚያሳካ ምርምር የሚያደርገባቸውን ዘዴዎች መቅረጽ አዲስ የ*ኡሰል አል-ፊቅሕ* እይታ ሲሆን የዘመኑን የሸሪዓ ሊቃውንት የጥናት ትኩረት የሳበ ርዕሰ-ጉዳይ ነው፡፡ በሸሪዓ ዓላማዎች *(መቃሲድ)* ላይ መሠረታዊ ግንዛቤ ለመጨበጥ፣ <u>አልዩ አባተ፣ የሸሪዓ ሕግ ዓላማዎች *(መቃሲድ አሹ-ሸሪዓሕ)፣* Bahir Dar University Journal of Law, Vol. 7 No. 2, pp. 261-281)</u> ያንብቡ፡፡

[13] Mohammad Hashim Kamali, Principles of Islamic Jurisprudence, Cambridge፡The Islamic Texts Society, 1991, p. 366.

[14] *ኢጅቲሓድ፣* በስፋት ከሚስተጋባው ኢስላማዊ *‹ጂሓድ›* ጋር፣ ከአንድ *ሥርወ-ቃል* የተወሰደ ሲሆን፣ *ኢጅቲሓድ* አዕምሯዊ ምርምርንና ጥረትን ሲወክል፤ *ጂሓድ* ደግሞ በብዙኃኑ ዘንድ ‹‹ቅዱስ ሃይማኖታዊ ጦርነት›› ከሚለው ትርጓሜው በሰፋ ሁኔታ የአምላክን ቀረቤታ ለማግኘት እና የሰውን ልጅና ማህበረሰብ ለማገልገል የሚደረግ እና ሐቁን ለማሳየት የሚደረግ ጥረት ሁሉ *ጂሓድ* (ጥረት፣ ትግል) ይባላል፡፡ ሁለቱም ቃሎች በተለያየ መንገድ እዉነቱን አጉልቶ ለማሳየት እና መልካም እሴቶችን ለመትከል የሚደረጉ ትይዩ ጥረቶች ከመሆናቸው አንጻር ተመሳሳይ ናቸው ሊባል ይችላል፤ ከዚህ አተያይ አንጻር፣ *ኢጅቲሓድ* የ*ጂሓድ* መቀናጀ ነው *(Ijtihad is the ally of jihad)* በማለት ይገልጹታል፡፡ (Taha Jabir Al-Alwani On Issues In Contemporary Islamic Thought፣ The International Institute Of Islamic Thought፣ 2005፣ pp. 66-67). በዚህ ረገድ የሚነሱ ነጥቦችን ለመቃኘት የሙሀመድ ሀሽም ከማሊን፣ Issues in the Understanding of Jihad and Ijtihad፣ Islamic Studies, Vol. 41, No. 4 (2002), pp. 617-634 ይመለከቷል::

[15] Kamali, Principles, *supra* note 13, p. 367.

[16] Ibid.

አመክንዮኣዊ በሚል የሚደረገው የሸሪዓ ምንጮች ክፍፍል ለጥናት አመቺነት እና መልክ ለማስያዝ ካለሆነ በስተቀር ተጨባጭ ልዩነትን አያመላክትም፡፡ አመክንዮኣዊ የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች መነሻቸው ከቁርአን እና ከ*ሱናሕ* በመሆኑ፣ በእነዚህ መርሆዎች መሠረት የሚቀረጹ ዝርዝር ሕግጋት በተዘዋዋሪ ከቁርአን እና ከ*ሱናሕ* የመነጩ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ እንደ *ኢጅማዕ* (የሊቃውንት ወጥ አቋም)፣ *ቂያስ* (ምስስሏዊ ድምዳሜ)፣ *ኢስቲህሳን* (ርትዕ)፣ የሕዝብ ጥቅም *(መስላሃሕ)* ወዘተ. የመሳሰሉ መርሆዎች በ*ኢጅቲሓድ* ስር የሚካተቱ እና በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት ከቁርአን እና ከ*ሱናሕ* ጋር የተዛመዱ ናቸው፡፡ በሸሪዓ ምንጮችና በ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች መካከል ያለው ልዩነት የቅርጽ መሆኑ አንዱ ማሳያ፣ የአንዱ መርሆ ጽንሰ-ሐሳብ ወሰን ከሌላው ጋር የሚቀላቀልበት እና በሁሉቱ መርሆዎች መካከል ግልጽ የልዩነት መስመር ለማስመር የሚቸግር መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የሊቃውንት *ሥምምነት* ሌሎቹን የ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች መሠረት ያደረገ ሊሆን ይችላል፤ ማለትም በ*ቂያስ* ወይም በ*መስላሃሕ* ላይ ተንተርሰው ሊቃውንት አንድ አቋም ሊያንጸባርቁ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ *ኢስቲህሳን*እና *ቂያስ* ተቀራረቢ ሐሳብ አላቸው፤ ከሁለት *ቂያሳዊ* ድምዳሜዎች መካከል አንዱ ለርትዕ አስፈላጊ ሆኖ ሊመረጥ ይችልና የ*ኢስቲህሳን* ቅርጽ ሊይዝ ይችላል፡፡ ባጠቃላይ በ*ኢጅቲሓድ* መርሆዎች መካከል ያለው ልዩነት በአብዛህኛው *ሥነ-ሥርዓታዊ* እንጂ የይዘት አለመሆኑን ይገነዘቧል፡፡[17]

*ኢጅቲሓድ* የሚደረግባቸው ጉዳዮች ቀድሞ በተገለጹ የሸሪዓ ምንጮች *ሥር* ያልተሸፈኑ ጭብጦች ላይ በመሆኑ፣ ተፈጻሚ ነው በሚል የተለየው ድንጋጌ *(ሁክም አሹ-ሸርዒ)* ትክክል ሊሆንም ላይሆንም ስለሚችል የአሻሚነት *(ዞኒ)* ደረጃ የሚይዝ ይሆናል፡፡ ስለሆነም *ኢጅቲሓድ* በተፈጥሮው አስገዳጅ ሊሆን አይችልም፡፡ *ኢጅቲሓድ* የሚያደርገው ግለሰብ በእውቀቱም ሆነ በምርምር አቅሙ ብቁ የሆነ ሊቅ *(ፈቂሕ)* መሆን አለበት፤ ይህ ግለሰብ *(ሙጅተሒድ)* ሙሉ አቅሙን አሟጦ ተጠቅሞ የመጨረሻ ነው የሚለው *ሁክም*ላይ እስካልደረሰ ድረስ፣ በግል የደረሰበት ድምዳሜ የአስረጂነት ዋጋ አይኖረውም፡፡ በተጨማሪም፣ የሸሪዓውን የሕግ አቋም ለመረዳት ከሕግ ባለሙያ በመጠየቅ ወይም አግባብነት ያላቸው የ*ፊቅሕ ሥራዎችን* በማጥናት *ሁክምን* ማወቅ *ኢጅቲሓድ* ሊባል አይችልም፣ ከዚህ ባህሪው *ኢጅቲሓድ* በግል እይታ ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያ ምርምርና እና ጥናት ማድረግ እንጂ የሌሎች *ሙጅተሒዶችን* ወይም *መዝሓቦችን* አቋም ማንጸባረቅ *ኢጅቲሓድ* እንደማይባል እንረዳለን፡፡[18]

*ኢጅቲሓድ* በዘፈቀዳዊ የግል እይታ ላይ እንዳይገነባ እና ተገማች *ሥርዓት* ይኖረው ዘንድ ሁለንተናዊ የጥናት ማዕቀፍ ተበጅቶለታል፤ ይኸውም *ኡሱል አል-ፊቅሕ* (የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች) ይባላል፡፡ *ኡሱል አል-ፊቅሕ* እንደ ጥናት መስክ ከጥንት ከነቢዩ *ሙሀመድ* ባልደረቦች በኋላ፣ በ*ታቢዑን* (ተከታይ የሙስሊም ማህበረሰብ( እንዲሁም ሰፋ ባለቅርጽ ደግሞ ከዚያ በኋላ በመጣው ትውልድ *(ታቢዕ አት-ታቢዑን)* መሠረታዊ ቅርጹን ይዞ፣ ከዚያ በኋላ በመጡት ተተካኪ ትውልዶች መሐከል በተነሱ የሸሪዓ ሊቃውንት ይበልጥ እየሰፋና የተለያዩ አተያዮችን እያዳበረ የመጣ የእውቀት ዘርፍ ነው፡፡ መስኩ፣ ከላይ እንደተወሳው፣ በጥቅል አነጋገር ከራዕያዊ ምንጮች ቀጥሎ የሚገኘውን፣ በዝርዝር የምንጮች ተዋረድ ደግሞ ሦስተኛ ላይ የሚገኘውን ምክንያታዊ የሕግ ምርምር ለመምራት የዋለ የአቀራረብ እና የዘዴ *(Methodology)* እውቀት ማዕቀፍ ነው፡፡[19] የ*ኢጅቲሓድ* ዘዴዎች ሲባል አንድም በቀዳሚ ምንጮች ውስጥ ያሉ የጥቅል የሕግ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም ሊመለከት ይችላል፤ በዚህ የሕግ ምርምር ዘዴ፣ የቁርአንና የ*ሱናሕ* ድንጋጌዎችን አተረጓጎም የሚመሩ ደንቦች በመስኩ ምሁራን ሊዳብሩ ችለዋል፡፡ ሌላኛው የ*ኢጅቲሓድ* ቅርጽ ደግሞ ትርጉም ሳይሆን ኢዲስ ሕግጋት የሚቀረጹባቸው መንደርደሪያ ንድፈ-ሐሳቦችን የሚመለከት ነው፤ ከእነዚህ የሕግ መርሆዎች መካከል ምስስሏዊ አመክንዮ *(ቂያስ)*፣ ርትዕ *(ኢስቲህሳን)*፣ የቀጣይነት ግምት *(ኢስቲስሃብ)* እና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡[20] ከቁርአን እና ከ*ሱናሕ* ቀጥሎ ያሉ የሸሪዓ መርሆዎች እና ምንጮች ሁሉ በ*ኢጅቲሓድ ሥር* የሚወድቁ ናቸው፡፡[21]

## 3. *ኢጅቲሓድ የሚደረግባቸው ጉዳዮች*

ከ*ኢጅቲሓድ* የትርጓሜ ክፍሎች መካከል አንዱ በተነሳው አዲስ ጭብጭ *(ፈርዕ)* ላይ የሚደረገው የሕግ ምርምር በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ላይ የመሠረተ ሊሆን የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ቀድመው በመለኮታዊ ራዕይ *(ወህይ)* የተገለጹ ሕጎችንና

[17] Ibid., pp. 366-367.
[18] Ibid., pp. 315-316
[19] Mohammad Hashim Kamali, Methodological Issues in Islamic Jurisprudence, Arab Law Quarterly, Vol. 11, No. 1 (1996), p. 3.
[20] Ibid.
[21] Ibid.

*መርሆዎችን መሠረት ያላደረገ ማንኛውም የሕግ ወይም ሌላ ምርምር ኢጅቲሓድ አይባልም፡፡* በኢጅቲሓድ የጽንሰ-ሐሳብ ወሰን ውስጥ የማይካተቱ የምርምር አይነቶች መካከል፣ ሙሉ በሙሉ ንድፈ-ሐሳባዊ *(ዐቅሊ)* የሆነ አመክንዮዊ ምርምር፣ በፍሬ-ነገር ወይም ሕዋሳዊ መረጃ ላይ ብቻ የተመሰረተ *(ሂሲ)* ተሞክሯዊ ምርምር፣ በልማድ ላይ የተመረኮዘ *(ዑርፊ)* ምርምር ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ስለፈጣሪ ህልዉና ወይም ስለ *ሥነ*-ፍጥረት መነሻ የሚደረግ ምርምር በንድፈ-ሐሳብና በተጨባጭ እውነታዎች ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ኢጅቲሓድ አይባልም፡፡ ስለሆነም፣ በቀዳሚ ምንጮች ውስጥ በቀጥታ ያልተዳሰሱ የሕግ ጉዳዮች ላይ አንድ ለአካለ-መጠን የደረሰን ሰው ምግባር እና ባህሪ የሚገዙ ዝርዝር ሕግጋትን ለማውጣት የሚደረግ ኢጅቲሓድ በቁርአን እና/ወይም በ*ሱናሕ* ቀድመው የተደነገጉ መለኮታዊ ድንጋጌዎችን ወይም የሕግ መርሆዎችን ያጣቀሰ *(ኢስቲንባጥ)* መሆን ይኖርበታል፡፡ በቀዳሚ የሸሪዓ ምንጮች ያልተመራ፣ በ*ወህይ* ማዕቀፍ *ሥር* ያልሆነ የትኛውም ምርምር ኢጅቲሓድ የማይባል መሆኑን ይገነዘቧል፡፡[22]

በቁርአንና *ሱናሕ* በግልጽ ተለይተው በተዳሰሱና ዝርዝር የሕግ ሽፋን በተሰጣቸው ጉዳዮች ላይ *(ኑሱስ)* ምርምር ማድረግ አስፈላጊ ባለመሆኑ፣ እነዚህ ጉዳዮች ለኢጅቲሓድ ተገዢ አይደሉም፡፡[23] በቁርአን እና *ሱናሕ* የተካተቱ የሕግ አስረጂዎች *(አዲላሕ)* ለኢጅቲሓድ ካላቸው አግባብነት አንጻር ለአራት ተከፍለው ሊታዩ ይችላሉ፦[24]

### i. የተዓማኒነት እንከን ወይም የግልጽነት ችግር የሌለበት አስረጅ

የቁርአን ወይም የ*ሱናሕ* አስረጂው የተዓማኒነት ወይም የግልጽነት ችግር የሌለበት *(ኑሱስ)* ከሆነ ኢጅቲሓድ ሊደረግበት አይችልም፡፡ ለምሳሌ፦ በወራሾች መካከል ያለውን የውርስ ድርሻ የሚወስኑት የቁርአን ልዩ ድንጋጌዎች፣ ከግልጽነት አንጻር ለትርጉም ያልተጋለጡ በመሆናቸው ኢጅቲሓድ አይደረግባቸውም፡፡ ይህ በጥንታዊ የ*ፉሱል* አረዳድ የተረጋገጠ ቢሆንም፣ ቁርአን ወይም *ሱናሕ፣* በወንጀል፣ በቤተሰብ ወዘተ. ጉዳዮች ላይ ያካተቷቸው ዝርዝር ድንጋጌዎች ከወቅቱ ሕብረተሰብ አኳያ ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ከሆኑ የዘመኑን ማህበረሰብ ተጨባጭ እውነታዎች እንዲሁም የሸሪዓ ዓላማዎች *(መቃሲድ)* አንጻር እንደገና ሊቃኙ ይገባል በማለት፣ ሐሺም ከማሊን ጨምሮ ሌሎች የዘመኑ የሸሪዓ ሊቃውንት ይከራከራሉ፡፡[25]

### ii. ተዓማኒ የሆነ ነገር ግን የግልጽነት ችግር ያለበት አሻሚ አስረጅ

ቁርአን በጠቅላላው የተዓማኒነት እንከን የሌለበት *መሆኑ* በሁሉም ምሁራን ዘንድ የ*ታመነ* ነው፡፡[26] ነገር ግን የሕግ አንቀጾቹ ግልጽ ያልሆኑ ከሆነ ለትርጉም የተ*ጋ*ለጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ በ2፡228፣ ከፍቺ በኋላ፣ ሴቷ ለሦስት *‹ቁሩእ›* (የብቸኝነት ጊዜ) ሳታገባ እንድትቆይ ተደንግጓል፡፡ *‹ቁሩእ›* የሚለው ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም ያለው አሻሚ ቃል በመሆኑ አንቀጹን *ዞኒ* ያደርገዋል፤ በመሆኑም ለኢጅቲሓድ የተ*ጋ*ለጠ ያደርገዋል፡፡ *ቁሩእ* የሚለው ቃል የወር አበባ ወይም የንጽህና ጊዜያት በሚል ሊተረጎም ይችላል፡፡ አቡ-ሀኒፋና ኢብን-ሀንበል ‹የወር አበባ› በሚል ሲተረጉሙት አሽ-ሻፊዒ እና ማሊክ ደግሞ ‹ሦስት የንጽህና

[22] Kamali, Principles, *supra* note 13, p. 368

[23] *ዝርዝር ቁርአናዊ ወይም የሱናሕ ድንጋጌዎች ባረፉባቸው የፍትሐ-ብሔር ወይም ወንጀል ጉዳዮች ላይ ኢጅቲሓድ ማድረግ ተገቢነት የለውም የሚለው በመርሕ ደረጃ የማይካድ ቢሆንም፣ ከኢጅቲሓድ መርሆዎች መካከል አንዱ የሆነው የርትዕ ወይም አፈጻጸም ምርጫ (ኢስቲህሳን) ልዩ የቁርአን ወይም የሱናሕ ድንጋጌዎችን ተግባራዊ በማድረግ ሒደት ውስጥ አስከፊ ወይም አፍራሽ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ፣ ዳኛው የአፈጻጸሙን ቅርጽ እንዲለውጥ የሚፈቅድ መርሆ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ከግልጽነታቸው አንጻር ለኢጅቲሓድ ያልተጋለጡ የሚመስሉ የሕግ ጉዳዮች ሌላው ቢቀር በአፈጻጸማቸው ረገድ ኢጅቲሓድ ሊደረግባቸውና ለውጥ ሊደረግባቸው እንደሚችል የኢስቲህሳን ጽንሰ-ሐሳብ አስረጂ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አንዳንዳድ ቁርአናዊ የውርስ እና የወንጀል ድንጋጌዎች ግልጽ ከመሆናቸው አኳያ የሕግ ትርጉም የማያስፈልጋቸው በመሆኑ በቀጥታ ለአፈጻጸም ዝግጁ ናቸው ቢባልም እንኳ፣ የሸሪዓ ዓላማዎች (መቃሲድ) እና ዘመነኛ የፉሱል እይታዎች ማቆጥቆጣቸውን ተከትሎ በእነዚህ ልዩ ድንጋጌዎች ላይም ቢሆን በኢስቲህሳን አማካይነት በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ከሚደረገው የአፈጻጸም ለውጥ በተጨማሪ፣ ጥቅል የአፈጻጸም እገዳ ሊጣልና በምትካቸው የሕብረተሰቡን አወቃቀርና እሳቤ ያገናዘቡ አዳዲስ የቤተሰብ እና የወንጀል ድንጋጌዎችና ቅጣቶች የሚቀረጹበት ሸሪዓዊ መሠረት እንዳለ የዘመኑ የሸሪዓ ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡ ለአብነት ያህል ጣሪቅ ረመዳን፣* Has political Islam failed? Head to Head [Al Jazeera English](https://www.youtube.com/watch?v=KlVHPflOljY)፣ published on Apr 22, 2016 https://www.youtube.com/watch?v=KlVHPflOljY *ይመለከቷል፡፡*

[24] Kamali, Principles, *supra* note 13, pp. 316-317.

[25] Ibid., pp. 173-174

[26] Ibid., p. 11

ወቅቶች› በሚል ተርጉመውታል፡፡ በዚህ *የኢጅቲሓድ* ልዩነት ምክንያት የተለያየ የብቸኝነት ጊዜ አቆጣጣር እና የውጤት ልዩነት ይገኛል፡፡

### iii. ተዓማኒነቱ አጠራጣሪ ሆኖ በመልዕክቱ አሻሚ የሆነ አስረጅ

ይህ አይነቱ አስረጂ የሚገኘው ሁለተኛ የሸሪዓ ምንጭ በሆነው በ*ሀዲስ* ላይ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ተዓማኒነቱ አከራካሪ ሆኖ የግልጽነት ችግር ሊኖርበት የሚችለው *ሀዲስ* ብቻ ነው፡፡ በ*ሀዲስ* የዘገባ *ሥርዓት* ተላልፈው ለመጨረሻው ትውልድ የደረሱት *ሀዲሶች፣* ከጥቂቱ በስተቀር ሁሉም ማለት ይቻላል በአንድ የነቢዩ ባልደረባ በኩል የተላለፉ - *አሀድ* (ነጠላ) ዘገባዎች ናቸው፡፡[27] *አሀድ* ዘገባዎች በአንድ የዘገባ ሰንሰለት ብቻ የወረዱ በመሆናቸው ተዓማኒነታቸው አጠራጣሪ *(ዞኒ)* ነው፡፡ እነዚህ *ሀዲሶች* በይዘታቸው ግልጽ ቢሆንም ከተዓማኒነት አኳያ (ከአስተላላፊዎቹ *ታማኝነት* ወይም የዘገባው ቀጣይነት *(ኢስናድ)* አንጻር *ኢጅቲሓድ* ሊደረግባቸው ይችላል፡፡ በ*አሀድ* ዘገባዎች ላይ ምሁራን ተፈጻሚ የሚያደርጓቸው *የታማኝነት መመዘኛዎችና* የሚሰጧቸው የተዓማኒነት ደረጃ የተለያየ በመሆኑ በአስረጂነታቸው ላይ የተለያየ *ኢጅቲሓድና ሁክም* (ፍርድ) ላይ ይደርሳሉ፡፡ [28]

### iv. በተዓማኒነቱም እና በፍሬ-ሐሳቡ አከራካሪ የሆነ አስረጅ

ይህም ቢሆን በ*ሱናሕ* ላይ ብቻ የሚገኝ የአስረጅ አይነት ሲሆን፣ አንድ *ሀዲስ* በአዘጋገቡ *አሀድ* (ነጠላ) ሆኖ በፍሬ-ሐሳቡ ደግሞ አሻሚ በሚሆን ጊዜ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ *ያለ ሱራሕ አል-ፋቲሃሕ ሶላሕ የለም (ላ ሶላተ)* የሚለው *የሀዲስ* ዘገባ ነጠላ ከመሆኑ በተጨማሪ *‹ላ ሶላተ›* የሚለው አገላለጽ፣ *ፋቲሃ* ሳይነበብ ቢቀር ውጤቱ *ሥግደቱን* ውድቅ ማድረግ ይሁን ወይስ ጽኑእነቱ እንደተበጠቀ ሆኖ *ሥርዓቱ* ጎዶሎ እንዲሆን ብቻ ማድረግ ይሁን ግልጽ አይደለም፡፡ እንደ አሽ-ሻፌዒ እይታ *ፋቲሃ* ባልተነበበበት *ሥግደቱ* ዋጋ የለውም ሲሉ፣ *ሀነፊዎች* ደግሞ *ሥግደቱ* እንከን ያለበት እንጂ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አይሆንም የሚል አቋም አላቸው፡፡[29]

ባጠቃላይ፣ *ኢጅቲሓድ* ሁለት አይነት ቅርጽ ሊይዝ ይችላል፣ አንደኛው የትርጉም ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሕግ የማውጣት ነው፡፡ በቀዳሚ ምንጮች *(ኑሱስ)* ውስጥ ያሉትን አስረጂዎች ከላይ በተገለጹት አኳኋን *ዞኒ* በሚሆኑ ጊዜ *ኢጅቲሓድ* የትርጉም ቅርጽ ይኖረዋል፡፡ በተያዘው ጭብጥ ላይ ምንም አይነት አስረጂ የሌለ ከሆነና ጉዳዩ ሙሉ በሙሉ ያልተሸፈነ ከሆነ፣ *ኢጅቲሓድ* አዲስ ሕግጋትን የመቅረጽ ሚና ይኖረዋል፡፡[30] አዲስ የሕግ ጭብጦች ላይ ዝርዝር ሕግጋት የሚቀረጹት በ*ኢጅቲሓድ መርሆዎች* ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ ከእነዚህ *መርሆዎች* መካከል *ቂያስ፣ ኢስቲህሳን* እና *መስላሃሕ* የሚገኙበት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት አራት ሸሪዓዊ የአስረጂ አይነቶች መካከል፣ *ኢጅቲሓድ* በመጀመሪያው (i) ላይ ተፈጻሚ የማይሆን ሲሆን፣ በቀሪዎቹ ማለትም ከ **ii-iv** በተጠቀሱት የአስረጂ አይነቶች ላይ ሊተገበር ይችላል፡፡[31]

## 4. *ኢጅቲሓድ* የማድረግ ሸሪዓዊ ግዴታ

*ኢጅቲሓድ* ማድረግ በሸሪዓ እይታ ያለው የግዴታ ደረጃ ምን ያህል ነው ለሚለው ጥያቄ፣ እንደ ጭብጥ በተነሳው የሕግ ጉዳይ የአንገብጋቢነት ደረጃ ላይ የሚወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአፋጣኝ ምላሽ የሚያሻው ጉዳይ ከሆነ፣ ሁልጊዜ የሕብረተሰብ የሸሪዓ ሊቆች *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ሸሪዓዊ ብይን *(ሁክም)* የመስጠት ግለሰባዊ ግዴታ *(ፈርድ ዐይኒ)* አለባቸው፡፡ በተለይ ደግሞ ብዙ *ሙጅተሒዶች* በሌሉበት ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኝ *ሙጅተሒድ፣* አስቸኳይ የሕግ ምላሽ የሚያሻው ጉዳይ ካጋጠመ፣ ምርምር የማድረግ ግለሰባዊ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ አጣዳፊ ካልሆነ በዚህ አይነቱ ጉዳይ ላይ ሁሉም የሕብረተሰቡ *ሙጅተሒዶች*

---

[27] አልዩ አባተ፣ *ሱናሕ፦ ሁለተኛው የሸሪዓ ሕግ ምንጭ፣* Hawassa University Journal of Law, Vol. 2, p. 185 (2018). የዚህ ጽሁፉ አጠቃላይ ይዘት የሀዲስ ተዓማኒነትን ጥያቄ ውስጥ ያስገቡ ታሪካዊ ምክንያቶች ላይ፣ በመስኩ ሊቃውንት በተዘረጋው የተዓማኒነት ምዘና *ሥርዓት* ላይ፣ የሀዲስ አስረጂነት ደረጃዎች እና ሌሎች ከሀዲስ ዘገባዊ ምንጭነት እና የ*ሱናሕ* አስረጂነት ጉዳዮች ላይ መሠረታዊ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

[28] Kamali, Principles, *supra* note 13, pp. 368-369

[29] Ibid., p. 369

[30] Ibid.

[31] Ibid., p. 368

ምርምር በማድረግ የሕግ መፍትሔ የማበጀት *የጋራ ግዴታ (ፈርድ ከፋኢ)* አለባቸው፡፡ *ዋጂብ ከፋኢ* አለባቸዉ ሲባል ግዴታዉ ባሉት *ሙጅቲሒዶች* መካከል በአንዱ ከተከወነ የሁሉም ሊቆች ግዴታ ይወርዳል፡፡ *ሙጅቲሒዱን* በግል የሚመለከተው ጉዳይ ከሆነ፣ *ኢጅቲሓድ* በማድረግ የራሱን አቋም የመያዝ እና የመከተል ግዴታ *(ዋጂብ ዐይኒ)* ሲኖርበት፣ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌሎች *ሙጅቲሒዶች* ያላቸውን *ፊቂሓዊ* አቋም መከተል *(ተቅሊድ)* አይፈቀድለትም፡፡ ተከታይነት ለተራው ሕዝብ እንጂ ከምንጮች ላይ ተንተርሶ የራሱን የሕግ ምርምር በማድረግ *ሁክም* ላይ መድረስ ለሚችል *ሙጅተሒድ* አይፈቀድም፡፡ በተጨማሪም አንድ ልዩ ጉዳይ ለአንድ *ሙጅተሒድ* ወይም ዳኛ *(ቃዲ)* የተመራ በሆነ ጊዜ፣ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ የ*ሙጅተሒዱ* ግለሰባዊ ግዴታ ይሆናል፡፡[32]

*ኢጅቲሓድ* ግዴታ *(ዋጂብ)* ባልሆነባቸው ሁኔታዎች ላይ ሁሉ የሚበረታታ *(መንዱብ)* ይሆናል፤ ማለትም ጉዳዩ አጣዳፊ ባልሆነበት ወይም ሌሎች *ሙጅተሒዶች* ባሉበት ማህበረሰብ ውስጥ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ *ዋጂብ ከፋኢ* (ማህበረሰባዊ ግዴታ) ነው፡፡ የተነሳው የሸሪዓ ጭብጥ በተጨባጭ ያላገጠመና ንድፈ-ሐሳባዊ ብቻ በሆነ ጊዜ፣ በእነዚህ መላምታዊ ጉዳዮች ላይ ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር ማድረግ የሚበረታታ ነው፡፡[33]

እንደ ጭብጥ ሆነዉ የሚነሱት የሕግ ጉዳዮች በቁርአን ወይም *ሱናሕ* ውስጥ ተለይተው ግልጽ ድንጋጌ ያረፈባቸው ከሆነ፣ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ የ*ኢጅቲሓድ* ዓላማ ግልጽ የሸሪዓ ሽፋን ባላገኙ ጉዳዮች ላይ ከቀዳሚ ምንጮቹ ያልራቀ የሕግ ምርምር በማድረግ ፍትሓዊ የሸሪዓ ሥርዓት መዘርጋት እንጂ፣ ግልጽ መለኮታዊ ድንጋጌዎችን ወደ ጎን በማለት ከመለኮታዊ ቁጥጥር እና አመራር ውጭ የሆነ የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽ አይደለም፡፡[34]

አንድ *ሙጅተሒድ* በአንድ የሕግ ጭብጥ ላይ *ኢጅቲሓድ* አድርጎ የራሱ ድምዳሜ ላይ ከደረሰ በኋላ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ሌሎች *ሙጅተሒዶች* የያዙትን አስተያየት መከተል እንደማይፈቀድለት ሁሉም የ*ኡሱል ዑለማእ* ይስማሙበታል፡፡ *ኢጅቲሓድ* ያልተደረገባቸው ጉዳዮች ቢገጥሙት እንኳ ሌሎች የደረሱበትን *ሁክም* ከመከተል ይልቅ የራሱን *ኢጅቲሓድ* እንዲያደርግ ይገደዳል የሚል አስተያየት በብዙሓኑ ዘንድ ተንጸባርቋል፡፡ ይህም ምንጮችን ተንተርሶ የራሱን የሕግ ምርምር ማድረግ የሚችል አማኝ ሁሉ ምርምር እንዲያደርግ የሚበረታታ መሆኑንና ሌሎችን በጭፍን ከመከተል *(ተቅሊድ)* ይልቅ ግላዊ እሳቤን በመጠቀም የተያዘ አቋም ከውስጣዊ እምነት የመነጨ በመሆኑ፣ ትግበራውም ቢሆን ቀላልና ፍሬያማ እንደሚሆን ያመለክታል፡፡ *ተቅሊድ* የሚፈቀደው *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ለማይችል ለተራ አማኝ *(ዐሚ)* ብቻ ነው፡፡

*ኣንድ ሙጅተሒድ* በአንድ ወቅት የያዘውን *ኢጅቲሓዳዊ* አቋም፣ በሁኔታዎች መለወጥ ምክንያት ወይም የተለየ አረዳድ በመያዙ ምክንያት የመቀየር ሙሉ ነጻነት እና ግዴታ አለበት፡፡ በዳኝነት መደብ ላይ የሚገኙ *ሙጅተሒዶች* ከሆኑ በሚሰጡት ፍርድ መካከል የበላይና በታችነት የለም ምንም እንኳ በዘመናዊ የፍርድ ቤት አደረጃጀት የይግባኝ ሥርዓት ሊኖርና የበታች ፍ/ቤት ውሳኔዎች በበላይ ፍ/ቤቶች ሊሻር ወይም ሊታረም ቢችልም፣ ይህ ሲባል በመርህ ደረጃ በዳኛ *ሙጅተሒዶች* መካከል ያለው ሸሪዓዊ አስተያየት የተለያየ የአሳማኝነት ደረጃ ሊኖራቸው ቢችልም፣ በዚህ መመዘኛ አንዱ ከሌላው ሊመረጥ ቢችልም፣ *ኢጅቲሓድ* በአስረጂነቱ *ዞኒ* (አሻሚ/ወሳኝ ያልሆነ - *Speculative)* በመሆኑ፣ በምሁራዊ ወይም በዳኝነት *የኢጅቲሓድ* ድምዳሜዎች መካከል የበላይነትና የበታችነት የለም፡፡ ይህም *ኢጅቲሓድ* አስገዳጅ ባለመሆኑና እንደ ዳኛ አስተያየት (*ዞኒ* አስረጂ) እኩል የአስረጂነት ሚና ያለው በመሆኑ ነው፡፡[35] የ*ኢጅቲሓዳዊ* ድምዳሜዎች የአስረጂነት እኩልነት፣ ‹አንድ *ኢጅቲሓድ* በአምሳያው አይሻርም *(ኣል-ኢጅቲሓዱ ላ ዩንቀድ ቢሚስሊሒ)*› በሚለው የሸሪዓ ሕግ ቀኖና *(Legal Maxim)* ይወከላል፡፡[36]

## 5. የ*ኢጅቲሓድ* አስረጂነት (የሕግ ምንጭነት)

*ኢጅቲሓድ* የሸሪዓ ምንጭ መሆኑ በቁርአን፣ በ*ሱናሕ* እና በአመክንዮኣዊ አረዳድ *(ዐቅል)* የተደገፈ ነው፡፡ ከቁርአን ብንነሳ፣ በ*ሱራሕ* ኒሳእ 4፡59፣

---

[32] Ibid., pp. 369-370
[33] Ibid., p. 318
[34] Ibid., p. 370
[35] Ibid., p. 371
[36] Ibid., p. 372

> ‹‹እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የሥልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትሆኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት፡፡››[37]

በዚህ አንቀጽ የመጀመሪያው ዐረፍተ-ነገር፣ የሸሪዓ ወይም በአጠቃላይ የኢስላም የእውቀትና የሕግ ምንጭ፣ አምላክ በመልዕክተኛው በኩል የገለጸውን ቅዱስ ቃሉን - ቁርአንን፣ እና ነቢይ ሆነው የተላኩትን የሙሀመድን አረዓያነት - *ሱናሕ* መሆናቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡ ሁለተኛው የአንቀጹ ክፍል ደግሞ አንደ ጭብጥ ሆኖ በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ የተነሳ አንድ ጥያቄ ወይም ያጋጠመ ችግር ቢኖር፣ በቁርአንና *ሱናሕ* መሠረት መፍትሔ ሊያገኝ እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ይህ አገላለጽ፣ ነገሩ በቀጥታ በቁርአንና በ*ሱናሕ* ባይዳሰስ እንኳ በእነዚህ ቀዳሚ ምንጮች ውስጥ የተገለጹ መሪ የሕግ መርሆዎች፣ የድንጋጌ ምክንያቶች፣ የሕግ ዓላማዎችና ግቦችን መሠረት በማድረግ ሌሎች አዳዲስ ወቅታዊና ከባቢያዊ ችግሮችን መቅረፍ ይችላል፤ የ‹መመለስ› ትርጓሜው የሕግ ፍንጮችን እና መርሆዎችን ተንተርሶ ለችግሮች የሕግ መፍትሔ መቅረጽ ማለት ነው፤ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ በቁርአንና በ*ሱናሕ* የሕግ ክፍል ላይ ጥልቅ ምርምር በማድረግ በመሆኑ የ*ኢጅቲሓድን* አስረጂነት ያመለክታል፡፡ (ተመሳሳይ ሐሳብ በቁርአን፣ 2፡105 ይገኛል፡፡)[38]

*ኢጅቲሓድ* ከግልጽነት አኳያ ከቁርአን ይልቅ የ*ሱናሕ* ድጋፍ አግኝቷል፡፡ ‹የ*ሙዐዝ ሁዲስ*› በሚል በሚታወቀው እውቅ ዘገባ መሠረት፣[39] *ኢጅቲሓድ፣* ከቁርአንና ከ*ሱናሕ* ቀጥሎ የሚገኝ የሸሪዓ ምንጭ ወይም አስረጅ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ *ኢጅቲሓድ* በውጤቱ ምንም ቢሆን አላፊነትን አያስከትልም፤ እንደውም የ*ኢጅቲሓድ* ስሕተት ቢፈጸም ኃይማኖታዊ ምንዳ እንደሚያስገኝ *ሁዲሱ* ያስረዳል፡፡ ሌሎች የሃይማኖት ጥናት ማድረግ *(ተፈቁሕ)* በአምላክ ዘንድ በመልካም አይን የመታየት ምልክት እንደሆነ፣ እና ሌሎች እውቀትን መፈለግ አስረጂነቱንና ጠቃሚነቱን የሚያስረዱ የ*ሁዲስ* ዘገባዎች በሙሉ የ*ኢጀቲሓድ* አብነቶች ተደርገው ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡[40] *ኢጅቲሓድ* በየዘመናቱ ባሉት የኢስላም ሊቃውንት ሲተገበር የኖረ መሆኑ፣ ብሎም በሙሀመድ ባልደረቦች በአስረጂነት ጥቅም ላይ ሲውል እንደነበር የሚያስረዱ፣ በብዙ የዘገባ መስመር የተዘገቡ ተዓማኒ *(ተዋቱር)* ዘገባዎች መኖራቸው፣ በ*ኢጅቲሓድ* የእውቀትና የሕግ ምንጭነት ላይ ሊቀርብ የሚችል ታሪካዊ ደጋፊ ማስረጃ ተደርጎ ሊቀርብ ይችላል፡፡[41]

በመጨረሻም፣ የ*ኢጅቲሓድ* አስረጂነት በአመክንዮኣዊ እሳቤ የተደገፈ ነው፡፡ በቁርአንና በ*ሱናሕ* በግልጽ ያልተሸፈኑ አዳዲስ የሕግ ጭብጦች መፍትሔ ሊቀመጥላቸው እንደሚገባ አከራካሪ አይደለም፡፡ ከሕብረተሰቡ የሥልጣኔ ለውጥ ጋር ተያይዞ ለሚፈጠሩ አዳዲስ ጉዳዮች አግባብነት ያላቸው ዝርዝር የሕግ ድንጋጌዎችን መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግም፣ ቁርአንና *ሱናሕ* መሠረትነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሸሪዓ በ*ኢጅቲሓድ* አማካይነት ተራዝሞና ተዘርዝሮ ከጊዜ ሒደትና ከማህበረሰብ የሥልጣኔ ለውጥ ጋር ተያይዞ የመጡ ዘርፈ-ብዙ ችግሮችና የሕግ ጭብጦች ምላሽና መፍትሔ የሚሰጡ የሕግ ማዕቀፎች ሊዘረጉለት ይገባል፤ በውጤቱም ሸሪዓ ተለማጭነቱና ቀጣይነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ስለዚህ፣ *ኢጅቲሓድ* በንድፈ-ሐሳባዊም ሆነ በተጨባጭ አመክንዮኣዊ እሳቤ አስፈላጊነቱ የማይካድ ነው፡፡[42]

---

[37] ቁርአን፡- 4፡59፣ የቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም፣ ሸህ ሰይድ ሙሀመድ ሳቢቅ እና ሐጅ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997 ዓ.ል.

[38] Kamali, Principles, *supra* note 13, p. 373

ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ፣ ነገር ግን በተዘዋዋሪ መንገድ የ*ኢጅቲሓድ* አስረጂነትን (የሕግ ምንጭነትን) የሚያስረዱ *(ዘዋሒር)* በርካታ የቁርአን አንቀጾች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል፣ በ*ሱራሕ አት-ተውባሕ* (9፡122) በጦርነት ጊዜ ሁሉም የሕብረተሰቡ ክፍሎች መውጣት እንደሌለባቸው፣ ይልቁንም የመዋጋት አቅም ባይኖራቸውም እንኳ ወደ ኋላ ቀርተው የኃይማኖት እውቀት ማጥናት *(ሊየተፈቀኍ ፊ ዲን)* እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ፣ እነዚያ በኛ መንገድ ላይ የሚታገሉ/የሚጥሩ *(ወ ለዚነ ጃሓዱ ፊና* - 29፡69) የሚለው አገላለጽ ሃይማኖታዊ ጥናትና ምርምርን ያካትታል፡፡ ከእነዚህና መሰል የቁርአን አንቀጾች *(ዘዋሒር)* ላይ በመነሳት *ኢጅቲሓድ* ቁርኣናዊ መሠረት እንዳለው ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡

[39] Sunan Abu Dawud (Hasan’s Trans.), Vol. III, Hadith No. 3585 and 3585.

[40] Kamali, Principles, *supra* note 13, pp. 373-374

[41] Ibid., p. 374

[42] Ibid.

## 6. የኢጅቲሓድ ተከፋፋይነት

የኢጅቲሓድ ተከፋፋይነት ሲባል በአንድ የሸሪዓ ሕግ መስክ ላይ ብቻ የእውቀት ባለቤት የሆነ ግለሰብ፣ ባጠናበት ዘርፍ ላይ ብቻ ኢጅቲሓድ ማድረግ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ጽንሰ-ሐሳብ ነው፡፡ ከፊቅሕ የሕግ ዘርፎች መካከል፣ ለምሳሌ፣ በውርስ ወይም በንግድ ሕግ ላይ ልዩ አጥኚና ተመራማሪ በመሆን ሙጅቲሒድ መሆን ይቻላል፡፡ ይህ ማለት በአንድ የፊቅሕ መስክ ሙጅተሒድ ሆኖ በሌሎች ላይ ሙቀሊድ መሆን የሚቻል ከመሆን ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጭብጥ ነው፡፡ ብዙኃኑ ዑለማእ፣ ኢጅቲሓድ ተከፋፋይ አይደለም፤ ስለሆነም ኢጅቲሓድ ማድረግ የሚችለው ሊቅ በሁሉም የሸሪዓ ሕግ ዘርፎች ላይ ሰፊና ጥልቅ እውቀት ያለው፣ ሁለ-ገብ ምሁር መሆን ይገባዋል የሚል አስተያየት አንጸባርቀዋል፡፡ ከብዙኃኑ በተለየ፣ ጥቂት የማሊኪ፣ የሀንበሊ እና ዟሒሪ ሊቃውንት ደግሞ ኢጅቲሓድ ተከፋፋይ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡[43]

የኢጅቲሓድ አንድነት ሐሳብ ምናልባት፣ በቀደምት የሙስሊም ሥልጣኔዎች የማህበረሰቡ እድገት ደረጃ ውስብስብ መስተጋብሮች ያልነበሩት ከመሆኑ አኳያ አግባብነት ሊኖረው የሚችልና፣ አንድ ሙጅተሒድ በሁሉም የሸሪዓ መስኮች ላይ ብቁ ምሁር መሆን ይችል ይሆናል፡፡ ይህ በራሱ አከራካሪ አንደሆነ ቢታወቅም የኢጅቲሓድ አንድነት ሐሳብ ባለንበት ዘርፈ-ብዙና ውስብስብ የሕብረተሰብ ሥልጣኔ ደረጃ ላይ ከፍተኛ የመረጃ ፍሰትና ቴክኖሎጂ ምጥቀት ባለበት የሉላዊነት የዓለም ተጨባጭ ላይ አንድ ግለሰብ በሁሉም ዘርፎች እውቀት እንዲኖረው የማይጠበቅ መሆኑን ከማሊ ያስረዳሉ፡፡[44] በተጨማሪም፣ ከታች እንደተብራራው ሙጅተሒዶች ከኢጅቲሓድ ከሚያደርጉበት የእሳቤ እርከን አኳያ፣ መስራች/ቀዳሚ ኢጅቲሓድ (ኢጅቲሓድ ፊ ሸሪዕ)፣ በመዝሓብ (የሸሪዓ ት/ቤቶች) ሥር ያለ ኢጅቲሓድ፣ የአፈጻጸም/ልዩ ኢጅቲሐድ በተሰኙ ምድቦች የሚመደቡ መሆኑ፣ በኢጅቲሓድ የተከፋፋይነት ሐሳብ ላይ የተገነባ መሆኑን ከማሊ አክለው ይገልጻሉ፡፡[45]

እውቀትን ኢስላማዊ ማድረግ *(Islamization of Knowledge)* የዘመናችን ታላቁ የሥነ-እውቀት ንቅናቄ ነው፡፡ ይህ የምሁራን ንቅናቄ፣ ቁሰ-ዓለማዊ የሳይንስ እውቀት በኢስላም እውቀት ማዕቀፍ ሥር (*Tawhidic Epistemology)* እንደገና የሚያድግበት የጥናትና ምርምር ጅማሮ ነው፡፡[46] በተለያዩ ሳይንሳዊ የእውቀት ዘርፎች በመታገዝ የሕግ ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ተጨባጭ ሕብረተሰባዊና ሃገራዊ ችግሮች ላይ ዝርዝር የሕግ እና የአፈጻጸም ሥርዓት ለመዘርጋት በሁሉም የሳይንስ መስኮች ላይና የሕግ ዘርፎች ላይ ባለእውቀት መሆን የማይታሰብ ነው፡፡

በይዘቱ አዲስ (ኦርጅናል) እና ፍሬያማ ምርምር ለማድረግ ሁሉም የእውቀት ዘርፎችን ከማማተርና ከመነካካት አንዱን በጥልቀት ማጥናትና (ማድማት) ለሕግ ምርምር የበኩሉን እሴት በመጨመር ሙጅተሒዶች ምሁራዊ ግዴታቸውን መወጣት ይገባቸዋል፡፡ ስለዚህ የኢጅቲሓድ ተከፋፋይነት ከዘመኑ ሉላዊነት እና ሁለንተናዊ የመረጃ ሥርጭት እውነታ አኳያ የሚደገፍና ተመራጭ የሆነ ሐሳብ ነው፡፡ ሙጅተሒዱ የአንድ ሳይንስ ልዩ እውቀት ባለቤት ከመሆን በተጨማሪ የሸሪዓ ሕግ መርሆዎችና ዘዴዎች (ኡሱል) የተካነ መሆን ይገባዋል፡፡ ይህ ሲባል በሁሉም የዝርዝር ሕግጋት ክፍሎች (ፊቅሕ) ላይ ጥናት ማድረግ አለበት ማለት ሳይሆን ለሕግ ምርምር የሚረዳውን መሠረታዊ የሕግ መሠረተ-ሐሳቦችና መርሆዎች እውቀት ከያዘ በኋላ በአንድ የእውቀት መስክ ላይ ብቻ ሙጅቲሒድ ሊሆን ይችላል፡፡[47]

---

[43] Ibid., p. 378
የኢጅቲሓድ ተከፋፋይነትን ሐሳብ ከሚደግፉ ሊቃውንት መከካል አቡል ሁሰይን አል-በስሪ፣ አል-ገዛሊ፣ ኢብን አል-ሁማም፣ ኢብን ተይሚያሕ፣ እና ተማሪዎቻቸው ኢብን አል-ቀይም እና አሽ-ሸውካኒ ይገኙበታል፡፡ (ከማሊ፣ ገጽ፡. 378-379)

[44] Ibid., p. 379

[45] Ibid.

[46] Rosnani Hashim & Imron Rossidy, Islamization of Knowledge: A Comparative Analysis of the Conceptions of Al-Attas and Al-Faruqi, Intellectual Discourse, 2000, Vol. 8, No I, pp. 21-22. See also: Osman Bakar, The Identity Crisis of the Contemporary Muslim Ummah፡ The Loss of Tawhidic Epistemology as its Root Cause, Islam and Civilisational Renewal, Vol 3 No 4: July 2012.

[47] በኢጅቲሓድ ሥርዓት ውስጥ የሕግ ሊቃውንት (ሙጅተሒዶች) በአንድ የሳይንስ እውቀት ሊኖረው ስለማይችል የመስኩን ድጋፍ ማግኘት የግድ ይሆንበታል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ በየሳይንስ መስኩ ያሉ ምሁራን ደግሞ ኡሱል ግንዛቤ እስካላቸው ድረስ በየጥናት ዘርፋቸው ኢጅቲሓድ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህ አንጻር ኢጅቲሓድ ሁለት ቅርጽ ሊይዝ ይችላል፡- የሕግ ኢጅቲሓድ እና የሳይንስ እውቀት ኢጅቲሓድ፡፡ የሕግ ቁጥጥር በሚያስፈልጋቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ አግባብነት ባለው የሳይንስ እውቀት ላይ በመመርኮዝ፣ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ሕግ መቅረጽ ይቻላል፡፡ ለዚህም የሕግ ተመራማሪዎች (ሙጅተሒዶች) ለሕግ

## 7. ማጠቃለያ

የሸሪዓ ምንጮች በጥቅሉ ራዕያዊ (ተገለጸ) እና አመክንዮኣዊ (በምርምር የተደረሰበት) በሚል በሁለት ሊመደብ ይችላል፡፡ ራዕያዊ የሸሪዓ ምንጮች የሚባሉት አንደኛው፣ በቀጥታ ከአምላክ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ የተገለጸው መለኮታዊ ራዕይ - ቅዱስ ቁርአን ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ በፍሬ-ሐሳባዊ ምንጩ ከአምላክ ሆኖ አገላለጹ የሙሀመድ የሆነው፣ *ሱናሕ* ነው፡፡ ሦስተኛው የሸሪዓ ምንጭ *ኢጅቲሓድ* ነው፤ ይህም የቁርአንና የ*ሱናሕን* ይዘት መሠረት አድረጎ በቀጥታ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በአመክንዮኣዊ የሕግ ትንታኔ የሚሸፈኑበትን የምርምር ዘዴዎች የሚመለከት ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ የሸሪዓ እድገት ዘመናት የተመሠረቱት የሕግ ት/ቤቶች የተቀረጹት የ*ኢጅቲሓድ* ንድፈ-ሐሳቦች አጠቃላይ የቁርአንን የሕግ ፍልስፍና የሚወክሉ ሲሆን፣ ንደፈ-ሐሳቦቹ ዘመንና ትውልዶችን ተሻግረው በየወቅቱ ለሚነሱ አዳዲስ የሕግ ጭብጦች የሕግ መፍትሔ ለማበጀት መንደርደሪያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በተለይ በቁርአንና በ*ሱናሕ* ተለይተው የተቀመጡ ዝርዝር ድንጋጌዎች በቁጥር አናሳ በመሆናቸው፣ እና ቁርአንና *ሱናሕ* በዋናነት የሕግ ጠቅላላ መርሆዎችን የሚያቀርቡ በመሆኑ፣ ዘርፈ-ብዙ የሕግ ርዕሰ-ጉዳዮችን ለመግዛት ዋነኛው ሸሪዓ ምንጭ የሊቃውንት *ኢጅቲሓድ* ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እንደ ቀደምት የ*መዝኃብ* መስራቾች፣ በቀጥታ ከቁርአንና ከ*ሱናሕ* በመነሳት ኦርጅናል የሕግ መርሆዎችንና ድንጋጌዎችን መቅረጽ የሚችል የለም የሚል እሳቤ የዓለምን የሙስሊም ማህበረሰብ ለውድቀት የዳረገ፣ ለቀደመው የሸሪዓ እሳቤዎች ጭፍን ተገዥ *(ሙቀሊድ)* እንዲሆን ያደረገ፣ እንዲሁም የሸሪዓን እድገት የገታ መሠረት አልባ የሕግ ባህል ነው፡፡ የሸሪዓ ምሁራን ይህን ተጨባጭ እውነታ ለመቀየር እና የቀደመው የ*ኢጅቲሓድ* ባህል በሕግም ሆነ በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች ላይ ያለው ከፍተኛ የምንጭነት ሚና እንዲያንሰራራ ርብርብ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ጥረቱን ተከትሎ፣ በሙስሊም ሃገሮችና ሙስሊም ዜጎች የሚገኙባቸው የዓለም ሃገራት፣ ሸሪዓን ከወቅቱ የሙስሊም ማህበረሰብ አስተሳሰብና ነባራዊ እውነታ አኳያ እያጋጠሙ ላሉ አዲስ ጭብጦች እልባት ለመስጠት እና ነባር ድንጋጌዎችን ለማሻሻል ሲባል ሸሪዓዊ የሕግ ምርምር *(ኢጅቲሓድ)* በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፤ በተለይም *ኢጅቲሓድ* የሚያደርጉ እና ወቅታዊ የሸሪዓ ጥናት የሚያደርጉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጀምሮ እስከ አስገዳጅ ወይም ምክረ-ሐሳብ የሚያቀርቡ የ*ሙጅተሒድ* ምክር ቤቶች፣ ብሎም በሕግ አውጪ ደረጃ፣ ተቋማዊ ቅርጽ አግኝቶ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ፍ/ቤቶችና ዳኞች ራሳቸውን በማሻሻል የሕግ አረዳዳቸውና አተረጓጎማቸው ከዘመኑ *ኢጅቲሓድ* እድገት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣ በተለይም የሸሪዓን ተለማጭነት በመረዳት ከሃገራችን ማህበረሰብ እና ከሚቀርቡ ልዩ ጉዳዮች አንጻር *ኢጅቲሓድ* ማድረግ ይችሉ ዘንድ ራሳቸውን በእውቀት የማብቃት *ሥራ* መስራት ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም፣ ከሕገ-መንግሥታዊ ሰብዓዊ እሴቶች ጋር ተጻራሪ ናቸው የሚል *ሥጋት* በተፈጠረባቸው የሸሪዓ ቤተሰብ ድንጋጌዎች ላይ አስፈላጊውን *ኢጅቲሓዳዊ* ማሻሻያዎችን ለማምጣትና እና በዚህ ረገድ ወጥ የሆነ የሸሪዓ አተረጓጎም እንዲኖር ይቻል ዘንድ አንድ ማዕከላዊ የሸሪዓ *(ኢጀቲሓድ)* ምክር ቤት ወይም ብሔራዊ የ*ኢጅቲሓድ* ጥናትና ምርምር ማዕከል ማቋቋም ለችግሩ አይነተኛ መፍትሔ እንደሆነ አንደ ሱዳን፣ ማሌዥያ እና ፓኪስታን ያሉ ሃገሮች ተሞክሮ ያሳያል፡፡[48]

የሸሪዓ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበታች ፍ/ቤቶች ያለውን የሕግ አተረጓጎም ወጥ በማድረግ፣ እንዲሁም አስፈላጊውን *ኢጅቲሓድ* በማድረግ ማሻሻያ አዳዲስ የሕግ ምልከታዎች ሊዘርጋ የሚችል ቢሆንም፣ ከይግባኝ በዘለለ የሰበር *ሥ*ልጣን ያለው ስለመሆኑ የሚያመላክት የሕግ አንቀጽ በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጅ አልተመለከተም፡፡ ያም ሆኖ የበላይ ሸሪዓ ፍ/ቤቶች የይግባኝ *ሥ*ልጣናቸውን በ*ኢጅቲሓድ* የተመራ የሕግ አተረጓጎሞችን በመከተል ተግባራዊ ካደረጉት የሰበሩን ያህል የአስገዳጅነት ደረጃ ባይኖረውም ሸሪዓ ሕጉን ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣምና የዳኞች የ*ተቅሊድ* እሳቤዎችን በማረም፣ እንዲሁም ወጥ አተረጓጎም በማስፈን ረገድ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

---

*መርሆዎችና ዘዴዎች በተጨማሪ በአንድ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ አጀንዳ ላይ የመጨረሻውን የሳይንስ እውቀት መሠረት በማድረግ ሕግጋትን ይቀርጻሉ፤ ያስፈጽማሉ፤ ይህ ማለት በአንድ የሳይንስ መስክ ላይ ጥልቅ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል ማለት ነው፡፡ በዚህ የጥናት ሂደት ሕግ እና ሌሎች የሳይንስ መስኮች ተቆራኝተው የሚጠኑበትን አቀራረብ ይመለከታል፤ ለምሳሌ፣ ሕግ እና ኢኮኖሚ፣ ሕግ እና ጤና፣ ሕግ እና ቤተሰብ/ግለሰብ ወዘተ. ሁለተኛው ኢጅቲሓድ ቅርጽ ፍጹም ሳይንሳዊ የሚሆንበት ነው፡፡ እዚህ ላይ የኢጅቲሓድ ሚና ተገቢነት ያለው የሕግ ማዕቀፍ በመዘርጋት የግልና የሕብረተሰብ ባህሪና ምግባር መግራትና መምራት አይደለም፡፡ ይልቁንም ሳይንሳዊ እውቀት ኢስላማዊ መሠረቱን ሳይለቅ እና በኦሱስ ተደግፎ እንዲያድግ ለማድረግ የሚያስችል ምርምር ነው፡፡ ይህ የኢጅቲሓድ ገጽታ እውቀትን ኢስላማዊ ማድረግ (Islamization of Knowledge) እየተባለ በሚጠራው አዲስ ኢስላማዊ-ሳይንሳዊ የእውቀት ምርምር ላይ ዋነኛው የምርምር መሣሪያ ነው፡፡*

[48] Kamali, Sharia Law, *supra* note 8, p. 175, 237 & 253

በተጨማሪም፣ በሸሪዓ ፍ/ቤቶች ሊኖር የሚገባው *ኢጅቲሓድ* እንቅስቃሴ፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሸሪዓ ጥናትና ምርምር ሊታገዝ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ሸሪዓ ሕግ የነበረው ድርሻ፣ የየማህበረሰቡን የግልና የቤተሰብ ግንኙነት እንዲገዛ እና በዚህ ረገድ የሚነሱ ግጭቶች በሕጉ አማካይነት እንዲዳኙ ካገኘው አስገዳጅ ሕገ-መንግሥታዊ እውቅና በተጨማሪ፣ መንግሥት የሙስሊሙን ማህበረሰብ የወለድ-ነጻ የባንክ አገልግሎት ፍላጎት ለማርካት የተከተለውን አበረታች የፖሊሲ ውሳኔ ተከትሎ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በ2011 (እ.አ.አ) ባወጣው *መመሪያ መሠረት*፣[49] በሃገሪቱ እየሰሩ ያሉ ንግድ ባንኮች የወለድ ነጻ አገልግሎት እንዲያቀርቡ ሕጋዊ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በመመርያው በግልጽ እንደተመለከተው፣ የባንክ ሥራውን በመምራትና በመቆጣጠር ተፈጻሚ የሚሆነው ኢስላማዊ የፋይንስ ሕጎች እና ወጥ አሠራር ደንቦች እንደሆነ ተመልክቷል (አንቀጽ 2(2))፡፡ ይህም ሸሪዓ በኢትዮይያ የሕግ ሥርዓት ተፈጻሚ የሚሆንበትን ወሰን አስፍቶታል፤ ወደፊትም የዘርፉን እድገት ተከትሎ የተፋጻሚነት ወሰኑ እየሰፋ እንደሚሄድ መገመት ይቻላል፡፡ ቤተሰባዊ ግኙነቶችን እና ኢስላማዊ የባንክ ግብይቶችን የሚገዛው የሸሪዓ ሕግ ዋነኛ ምንጭ የአመክንዮኣዊ የሕግ ምርምር ወይም *ኢጅቲሓድ* እንደሆነ በዚህ ጽኍፍ አጽንኦት ተሰጥቶታል፡፡ ታዲያ የሸሪዓ የፍርድ ሥርዓቱን እና የወለድ ነጻ የባንክ ሥራውን በማጠናከር፣ በማሻሻል እና በማስፋፋት ረገድ፣ እንዲሁም *ኢጅቲሓድ*ና ሌሎች የሸሪዓ ምንጮችን ከሃገራዊ እና ማህበረሰባዊ እውነታዎች ጋር አጣምሮ በማጥናት ተግዳሮቶችን መለየትና መፍትሔዎችን በመጠቆም ረገድ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ቀዳሚውን ድርሻ ሊይዙ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ያለውን የሸሪዓ ሕግ ትምህርት አቀራረብ ስናይ፣ የኢስላም ሕግ (*Islamic Law*) አማራጭ የትምህርት አይነት *(elective course)* ተደረጎ ለቅድመ-ምረቃ የሕግ ተማሪዎች በመሰጠት ላይ ይገኛል፡፡ የሸሪዓ የፍትሕ ሥርዓቱን *ኡሱል* እና *ፊቅሕ* ጥናቶች በሰለጠኑ ባለሙያዎች ይመራ ዘንድ፣ እንዲሁም የወለድ-ነጻ የባንክ ቁጥጥሩ እና አገልግሎቱ በሰለጠነ የሰው ኃይል መራመድ ይችል ዘንድ ከጀርባ ያለው የሃገራችን የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ተፈላጊውን ብቁ ባሙያዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ በሕግ ትምህርት መስክ የሚሰጠው የሸሪዓ ሕግ ትምህርት በይዘቱም ሆነ በአቀራረቡ መሠረታዊ ማሻሻያ ሊደግርበት ይገባል፡፡ ስለ *ኢጅቲሓድ* ምንነትና መገለጫዎች፣ እንዲሁም ለዝርዝር የቤተሰብ እና የፋይናንስ ሕጎች መሠረት የሆኑ የሸሪዓ መሠረተ-ሐሳቦች የሚያጠናው *ኡሱል አል-ፊቅሕ (Islamic Jurisprudence)* እውቀት ዘርፍ ራሱን ችሎ ሊቀርብ ይገባል፡፡ የሸሪዓ ኢስላማዊ የግልና የቤተሰብ ሕግ *(Islamic Personal and Family Law)፣* እና የፋይናንስ ዝርዝር ሕጎች ጥናት *(ፊቅሕ) (Islamic Finance and Banking Law)* ደግሞ ከ*ኡሱል* ጥናት ተነጥለው ለብቻቸው የሚሰጡበት የትምህርት ቀረጻ የቅድመ-ምረቃ የሕግ ትምህርት ሥርዓት አካል ቢደረግ በዘርፉ በተጨባጭ እያጋጠሙ ያሉ የብቃት እና የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ችግሮችን ማቃለል ይቻላል፡፡

---

[49] Directives to Authorize the Business of Interest Free Banking, Directive Number SBB/51/2011. Available at: http://www.nbe.gov.et/pdf/directives/bankingbusiness/sbb-51-11.pdf, Accessed on 10th April, 2017).